# ዕፀ ፋርስ በቤተ-መቅደስ?

ቃለ-ማዕነቅ ዘደብረ ዕንቍ

ስለ ዕፀ ፋርስ ጉዳይ እኔም የምለው አለኝ።

“የቄስ ሚስት ብትባል፤ ዕወቀች፣ ዐወቀች፣
ቆሸሸብኝ ብላ፣ መጽሐፉን አጠበች።” ይባላል።

መነሻ የሆነኝ “ማሪዋና በቤተ-መቅደስ?” በሚል ርዕስ (ቦጋለ ዳኜ) በኢትዮ ሚድያ ድረ-ገጽ ያወጡት ጽሑፍ ነው። አቶ ተስፋዬ ገብረ-አብ “የጋዜጠኛው ማስታወሻ” በሚል ርዕስ ከፃፉት አወዛጋቢ መጽሐፍ ጠቅሰው ነው ያስነበቡን። አቶ ተስፋዬ ለምን በቤተ-መቅደስ ጉዳይ እንደ ገቡ አልገባኝም። አማረብኝ ብለው በግምት ከፃፉዋቸው ሃላፊነት የጎደላቸው አስተያየቶች ውስጥ፣ አንዱ ይኸ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓተ-አምልኮ የሚያረክስ ቅጥፈት መሆኑን አንብበው ከታዘቡዋቸው መካከል አንደኛው ነኝ።

የወያኔ መደበኛ ካደሬ ሳሉ ይኸን መሰል ጽሑፍ ቢያወጡ አያስደንቅም ነበር። ምክንያቱም በደርግም ሆነ በወያኔ ሥርዓት የተነሱ ካደሬዎች ዋናው ሥራቸው ሃይማኖትን መገዝገዝ ሥለነበረ ያልቀባጠሩት ነገር የለም። “Religion is the opium of the people.” (ሃይማኖት የህዝብ አፍዝ አደንግዝ ነው።) የሚለውን አለቃቸውን የሌኒን ትምህርት የመሥበክ ግዴታ ስለነበረባቸው ነው። አቶ ተስፋዬ ግን አሁን ከዚያ ሁሉ ተፅዕኖ ነፃ ወጥቻለሁ እያሉ እና አበይት የሀገር ጉዳዮችን እየተነተኑ ለምን በማን አለብኝነት ከዚህ ስህተት እንደተዘፈቁ አይገባኝም። እውነተኛ ጸሐፊ ቢሆኑ ኖሮ፣ ፓትርያርክ መርቆርዮስ በነክንፈ ግፊት ከአገር መውጣታቸውን አውቃለሁ ካሉ፣ ለምን በቅርብ በሚያውቁት መረጃ ማን ከስልጣን እንዳወረዳቸውና የራሱን ሰው ከህግ ውጪ እንደጎለተ አልፃፉም?

በተከበሩት ገዳማት “በአክሱምና ዝቋላ በማሪዋና ይቆረባል” ብሎ የሃሰት ምስክር መሆን እውን ዓላማው ምንድነው? ይህ አባባል ጸሐፊው አማኝ ከሆነ ሃጢአት፣ ኢአማኝ ከሆነም ከባድ ወንጀል ነው። ቆርቦም ሆነ አቁርቦ የማያውቅ ምዕመን ባልቀመሰው ነገር ምስክርነት መስጠት ቀውስነት ነው። ምናልባት ደራሲው ዓመል ኖሮበት የተባለውን ቀማምሶ ወደዚያ የተቀደሰ አካባቢ ሄዶ ከሆነና የሚበላው፣ የሚጠጣው፣ የሚሸተተውም ያን መስሎ ስለሚታየው ጤናው ሲመለስለት ንሥሃ መግባት ይገባዋል እንጅ የሃሰት ምስክር መሆን የለበትም። ያለዚያ በሁለቱ ታላላቅ ገዳማት የሚያቆርቡትንም ሆነ የሚቆርቡትን የዕፀ ፋርስ ሱሰኞች አድርጎ ማቅረብ በጣም አስነዋሪ እና ሃላፊነት የጎደለው ተግባር ነው።

አሁን ቦጋለ ዳኜ ከገለጹላችሁ በተጨማሪ ስለ ዕፀ ፋርስ የማውቀውን ሃቅ ልግለጽላችሁ። ማሪዋና ማለት በትክክል ዕፀ ፋርስ ነው። አብሾ ወይም እኛ የምናውቀው አጤ ፋሪስ (አስተናግር) አይደለም። በሀገራችን፣ ዕፀ ፋርስ የድንብላል ተክል መስሎ የሚያድግና ቅጠለ ሰፋፊ ዕፅ ነው። ፍሬም ያፈራል። የሚበቅለውም

በማረሰ ቦታ ሲሆን በአንዳንድ ጠፍና ነባር ገዳማት ሳይዘራ በቅሎ እና ለምልሞ ይገኛል። ዕፀ ፋርስን ካዩትና ከቀመሱት መካከል አንዱ ስለሆንኩ ገቢሩን ልንገራችሁ። በቅኔ ትምህርት ቤት፣ ዕፀ ፋርስ የሚቀመሰው የጻጉሜን ሩፋኤል (የተርሆ ሰማይ) ዕለት ነው። በተለይ የቅኔ ተማሪዎች ቆጥረው ለመቀኘትም ሆነ ቅኔ ለመዝረፍ እንዲሠምርላቸው የዕፀ ፋርሱ ፍሬ ይወቀጥና በስንዴ ዱቄት ተገንፍቶ በትንሽ በትንሹ ይቀምሳሉ። የተማሪ ቤቱ (ጎጆ) ብርሃን እንዳያስገባና ጢስ እንዳያስወጣ በቅጠል ይሸፈናል። የዕፀ ፋርሱ ቅጠል ይጤስና ይታጠኑታል። እኔ የቀምስኩ ዕለት የተፈቀደልን ሶስት ስንሆን ወደ ቅኔ ትምህርት ቤት ከዘመዶቻችን ጠፍተን አንድነት የሄድን ቤተ-ዘመዶች ነበርን። እኔ የሰከርኩት በአንድ ጉርሻ ሲሆን የበረደልኝም በአንድ ቀን ጀምበር ነው። ግን ከሌሎቹ እኔ የ12 ዓመት ህፃን ነበርኩ። ሁለቱ እየተሻሙ ብዙ ስለበሉ ስካራቸው ያንዱ ሶስት ቀን፣ የሌላው ደግሞ አምስት ቀን ቆይቱዋል። ስሜታችንም የተለያየ ነበር። እኔ ያቀመሰንን የዘራፊያችንን ቅኔ ነጥቄያለሁ። (አንዱን ቤት ሲጨርስ ሁለተኛውን ቤት ቀማሁት ማለት ነው።) በሁዋላም የቅኔው ትምህርት ቀንቶኛል። የቅኔው ዘራፊ አስተማሪያችን በሁዋላ እንደነገሩን፣

"ኦ ራምኖን! ዘተሰመይኪ ፍቅርተ፣ (ብለው ሲጀምሩ)<br>
ወልድኪ ሐመልማለ-ሲና በመስቀል ሞተ።"

ብዬ እንደነጠቅሁዋቸው ከነቅኔው ነግረውኝ ይኸው እስከዛሬ ይዤዋለሁ። የቅኔው ትርጉም (የተወደድሽ ለምለም ዱግ ሆይ!) ብለው ሲጀምሩ (ልጅሽ የሲና ልምላሜ በመስቀል ሞተ።) ብዬ ሁለተኛውን ቤት ከነምሥጢሩ ነጠቅሁዋቸው ማለት ነው። ሲራቀቅም የዱግ ልምላሜ የሚጠወልገው በመስከረም የመስቀል ወራት ስለሆነ በእመቤታችን የተመሰለችውን ዱግ፣ ልጅሽ ልምላሜ በመስቀል ሞተብሽ ብዬ ተራቀቅሁ ማለት ነው። (ዱግ ማለት ከፍተኛ ዝናብ ሲዘንብ በደረቅ ቦታ በቅላ በመስከረም ወር የምትጠወልግ ለምለም ዕፅ ናት።)

ከቀምስነው መካከል አንዱ ጉዋደኛዬ በትሩን አንስቶ የአቁዋቁዋም ቀለም ይዘም ነበር። በሁዋላም ያቁዋቁዋም መምህር ሆኑዋል። ሶስተኛው ጉዋደኛችን ደግሞ (በቅሎይቱዋ አጋደለች! ጭነቱዋ ሊወድቅ ነው!) እያለ ይጮህ ነበር። የሚገርመው ነገር በሁዋላ ነጋዴ ሆኖ ቀረ። እንግዲህ ይኸ ሁኔታ እኔ የተሳተፍኩበትና ዕድሜ ልኬን የማልረሳው ጉዳይ ነው።

የዕፀ ፋርስ አብነት የሚቀመሰው በጥንቃቄና በአንድ ሰው ሕይወት ለአንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከተደጋገመ እንደሚያሳብድ የሚያቀምሱት ሰዎች ያስጠነቅቃሉ። ለሰመረለት ትምህርት ይገልጣል የሚባለው እውነት ነው፤ ደፋር ያደርጋልና። በተለይ ለንባብ ያሰልጣል። ለቅኔም ምሥጢርን ይገልፃል። በራሴ አይቸዋለሁ። ዕፀ ፋርስ ከመገንፋቱ በፊት ቀኑን ሙሉ ከመዝሙረ ዳዊት አሌ ፋቱ በሚቦካበት ውሃ ላይ ይደገማል። አንዳንድ ጊዜም በቅል የተቀመጠው ውሃ ይፈላል።

አቶ ተስፋዬ! በዝቋላም ሆነ በአክሱም ዕፀ ፋርስ ከቁርባን ጋር ይሰጣል ማለት ጸረ-ተዋህዶ ሃይማኖት ነው። በቅኔ ትምህርት ቤትም ቢሆን ይኸን ለአንድ ቀን የሚቀምሰው ተማሪ በበጎ ፈቃዱና በድብቅ ነው። ማታ ተማሪው ሁሉ ሲተኛ

ተጠንቅቆ ነው የሚቀመሰው። አንዳንድ መምህራን ለልጆቻቸውና ለዘመድ ልጆች በህፃንነት ያቀምሱዋቸዋል ይባላል። የእኛ ዋናው የቅኔ መምህር ግን ዕፀ ፋርስን ይቃወማሉ። እሳቸው ግን የሚታወቁበት ፍቱን የንባብ መድሃኒት ያውቃሉ። ለእኔ ግን ያን አላቀመሱኝም።

በነገራችን ላይ በብሪትሽ ቤተ-መፃሕፍት ከመቅደላ የተዘረፋና ሌሎችም ካሥር በላይ መፃሕፍተ-መዲሃኒት አሉ። ዕፀ ፋርስም ከመዲሃኒቶቹ አንዱ ሆኖ ☺ ተመዝግቡዋል። በተለይ ወንድነቱ ለተዳከመበት ይበጃል የሚል ተመዝግቦ ይገኛል። አወሳሰዱ ግን በጣም ጥንቃቄን ይጠይቃል። ያ ምናልባት ቪያግራ የሚባለውስ ከዚህ ሳይቀመም ይቀራል? የተረፈውን ለህክምና ጠበብት ለምርምር እተወዋለሁ።

በዕፀ ፋርስ (ማሪዋና) በፍጹም አይቆረብም። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት መርገም ነው። አቶ ተስፋዬ ይታረሙ። ያምርብኛል ብለው አገኝ ባጣውን ከመቀሳፈት ያርምሙ!